# የዜጎች መድረክ

ኢዜማ

ቅፅ 1 ቁጥር 23 ታህሳስ 9 ቀን 2012 ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ


## ከውጭ ድጋፍ ማግኘት መልካም ነው፤ ክትትሉ ግን ይጠንክር

## “ምርጫው የሚካሄድ ከሆነ አማራጭ መኖር አለበት ብለን ዝግጅት ጀምረናል” የሺዋስ አሰፋ

# የገቢ ማሰባሰቢያ የእራት መርሃ ግብር በስኬት ተጠናቀቀ ሂደት



# ከውጭ ድጋፍ ማግኘት መልካም ነው፤ ክትትሉ ግን ይጠንክር

ኢትዮጵያ የጀመረችውን ሁለገብ ማሻሻያ (ሪፎርም) ለማገዝ እና ሀገሪቷ ከገባችበት የአጠቃላይ ኢኮኖሚ ሚዛን መዛባት ለመታደግ የዓለም የገንዘብ ድርጅት (አይ.ኤም.ኤፍ) የ2.9 ቢሊዮን ዶላር ብድር ድጋፍ ስምምነት ላይ መደረሱና ለመጨረሻ የአይ.ኤም.ኤፍ ቦርድ ውሳኔ መቅረቡ ከዜናዎች ሰምተናል።

ይህ ድጋፍ በአሁኑ ወቅት ለኢትዮጵያ ጠቃሚ ነው ብሎ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ ፓርቲ (ኢዜማ) ያምናል። ይሁን እንጂ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ከዚህ በፊት የዕርዳታና ብድር አስተዳደርን በተለመከተ ያለው ልምድ ሲጤን ፓርቲያችን ያለውን ስጋት መግለጽ ይሻል።

ኢትዮጵያ ከዓለም ዓቀፍ ተቋማትና አገራት ከፍተኛ ብድርና ዕርዳታ ስታገኝ የቆየች ሀገር ናት። ኢሕአዴግ የመግሥትን ሥልጣን ከተቆጣጠረ ከ1983 ወዲህ መጠኑ ከፍተኛ የሆነ የውጭ እርዳታ አግኝታለች፤ ሆኖም ግን ሀገራችን ባገኘው ርዳታና ድጋፍ መጠን ያልለማች መሆኑ በገሀድ የሚታይ ሀቅ ነው። ፓርቲውና መንግሥት የተቀላቀሉበት የኢሕአዴግ አገዛዝ ዕርዳታዎች እና ብድሮችን ሲያስተዳድር የቆየው እንደ ፓርቲ ሀብት ጭምር ነው። በከፍተኛ መጠን የተገኘው የርዳታና የብድር ገንዘብ አለአግባብ ባክኗል፤ ከፊሉ የጥቂት ሹመኖች መክበሪያ ሆነዋል፤ ከውጭ ከገባው ያልተናነሰ ሀብት ከሀገር ወደ ውጭ እንዲሸሽ ምክንያት ሆነዋል። ባለፊት 28 ዓመታት በእርዳታና በብድር የገባው ገንዘብ አጠቃቀም በሚመለከት ወደፊት በዝርዝር መጣራት ይኖርበታል። በርካታ ፍሬ አልባ ፕሮጀክቶች ለዕርዳታና ብድር መጠየቂያነት ውለዋል የሚል እምነት አለ፤ አንዳንድ ፕሮጀክቶች ለብድርና መጠየቂያነት ብቻ ሲባል ታቅደው ሊሆን ይችላል። በእርዳታ ተጀምረው የወደቁ ፕሮጀክቶችን ዛሬ ከወደቁበት ማንሳት በራሱ ችግር ሆኗል፤ የሱኳር ፕሮጀክት ለዚህ ማሳየት ማንሳት ይቻላል።

ካለፉት ስህተቶቻችን መማር ይገባናል። ከውጭ ሀገራትና ድርጅቶች ርዳታም ሆነ ብድር ማግኘት ጥሩ ነገር ቢሆንም በተገኘው ሀብት አስተዳደር ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ካልተደረገ ከጥቅሙ ጉዳቱ ሊበልጥ የሚችል መሆኑ የራሳችን ልምድ ያስተምረናል። ስለሆነም ኢዜማ በአይ.ኤም.ኤፍ ድጋፍ አስተዳደር ላይ ጥብቅ ቁጥጥር እንዲደረግ ማስገንዘብ ይወዳል። የኢትዮጵያ ሕዝብም ብድር እና ዕርዳታ መገኘቱ ብቻ ሳይሆን በተገኘው ተሠርተው ያለው ሥራዎችን ማወቅ ይሻል። ስለሆነም ቁጥጥር ማድረግ ብቻ ክትትል ማድረግ ብቻ ሳይሆን የክትትሉን ውጤት ማሳወቅም ለሕዝብ ማሳወቅ ይገባል። ከዚህም በተጨማሪ የዋጋ ንረትን የመሰሉ ድጋፉ ሊያስከትላቸው ለሚችሉ ተጓዳኝ ጉዳቶች የመፍትሄ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ኢዜማ ያሳስባል።

# ኢዜማ በውጪ ሀገር ለሚገኙ የድጋፍ ማኅበራቱ አመራሮችን አስመረጠ

ታሕሳስ 08 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በ25 ከተሞች የዓለም አቀፍ የድጋፍ ማኅበሮችን አቋቋመ፡፡ የድጋፍ ማኅበሮቹ ከተቋቋመባቸው ከተሞች መሀል ፓሪስ፣ ፍራንክፈርት፣ ለንደን፣ ቴል አቪቭ፣ ናይሮቢ፣ ጆሀንስበርግ፣ ሜልበርን፣ አስሎ፣ ቶሮንቶ፣ አታዋ፣ ካልጋሪ፣ ኤድመንተን፣ ኪችነር፣ ዋሽንግተን ዲሲ፣ ሎስ አንጀለስ፣ ላስ ቬጋስ፣ ሴንት ሉዊስ፣ ዳላስ፣ ሂውስተን፣ ሲያትል፣ አትላንታ፣ ሮችስተርና አስቲን ይገኙበታል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ከተማዎች የየከተማዎቹ ድጋፍ ማኅበር አመራሮች ተመርጠው ሥራ የጀመሩ ሲሆን ሕዳር 27 ቀን 2012 ዓ.ም በተካሄደው የዓለም አቀፍ ሥራ አመራር፣ የሰሜን አሜሪካ ክፍለ ዓለም አስተባበሪ እና የዓለም አቀፍ የሥነ ሥርዓት ኮሚቴአባላትተመርጠዋል፡፡ለዜጎችመድረክ የደረሰው መረጃ እንደሚያመላክተውም ለዓለም አቀፍ ሥራ አመራር ሶስት ሰዎች ተመርጠዋል፡፡ በእዚህም መሰረት ታምራት ወርቁ ሊቀመንበር፣ ሚካኤል ደርቤ ጸሐፊ፣ ተስፋዬ ለታ የሂሳብ ክፍል ኃላፊ ሆነዋል፡፡ ለዓለም አቀፍ ሥነ ሥርዓት ኮሚቴም ሶስት ሰዎች የተመረጡ ሲሆን፣ መቅደስ ተለአለ፣ ወልደየሱስ ገብረማሪያም (ዶ/ር) እና ሳምሶን ሙሉጌታ ከተመረጡት አመራሮች መኻል ይገኙበታል፡፡ ለሰሜን አሜሪካ የክፍለ ዓለም አስተባባሪም ሳምሶን ሙሌጌታ ተመርጠዋል፡ ፡

የሌሎች ከተሞች ቻፕተሮችን የመመስረት ሂደት እና ያልተሟሉ የዓለም አቀፍ የሥራ አመራሮችንና የክፍለ ዓለማት አስተባባሪዎችን የማሟላት ሂደት እንደሚቀጥል የደረሰን መረጃ ያስረዳል፡፡





## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች
ለማኅበራዊ ፍትህ
(ኢዜማ)

ታህሳስ 9 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ኢዜማ ለሀገር አቀፍ ምርጫው ዝግጅት መጀመሩን ገለፀ

## “ምርጫው የሚካሄድ ከሆነ አማራጭ መኖር አለበት ብለን ዝግጅት ጀምረናል” የሺዋስ አሰፋ

ታኅሳስ 08 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)





የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) እሁድ ታሕሳስ 05 ቀን 2012 ዓ.ም በምርጫ ወረዳ 18 ሕዝባዊ ስብሰባ አካሄደ፡፡

በምርጫ ወረዳ 18 በተካሄደው ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ የኢዜማ አባላት፣ ደጋፊዎችና የወረዳው ነዋሪዎች ከፓርቲው የሥራ አስፈፃሚ አባላት ሊቀመንበሩ የሺዋስ አሰፋና የመንግሥት ትይዩ ካቢኔ እጩ ተወካይ ባንትይገኝ ታምራት (ዶ/ር) ጋር ውይይት አድርገዋል፡፡ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ወቅታዊ ሁኔታ ምን እንደሚመስልና ኢዜማ ከተመሰረተ ጀምሮ ምን ዓይነት እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ እንደቆየ ሊቀመንበሩ የሺዋስ አሰፋ ለስብሰባው ተካፋዮች ገለፃ አድርገዋል፡፡

ሊቀመንበሩ ለመወያየ የሚሆን ሀሳባቸውን ካካፈሉ በኋላ ከስብሰባው ታዳሚዎች የተለያዩ ጥያቄዎች ተነስተዋል፡፡ ኢዜማ ውስጥ ውስጠ ዴሞክራሲ አለ ወይ? አሁን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ኢዜማ ምርጫው ይካሄዳል ብሎ ያምናል ወይ? የመንግሥት ተፎካካሪ ሆናችሁ ከቀረባችሁ በመንግሥት በኩል እርምጃ እንደማይወሰድባችሁ ምን ዋስትና አላችሁ? በፓርቲያችሁ ውስጥ ከዚህ ቀደም በሌሎች ፓርቲዎች ላይ እንዳየነው ሌላ አላማ ያነገቡ ሰዎች ሰርገው እንዳይገቡባችሁ በምን መልክ ነው የምትቆጣጠሩት? የሚሉ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

ለተነሱት ጥያቄዎችም ሊቀመንበሩ የሺዋስ አሰፋ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በኢዜማ ውስጥ ውስጠ ዴሞክራሲ አለ ወይ? በሚል ለቀረበው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ ዴሞክራሲ ሂደት መሆኑንና ኢዜማ ከተመሠረተ በወራት የሚቆጠር እድሜ ያለው አዲስ ፓርቲ እንደመሆኑ መጠን ውስጠ ዴሞክራሲን አስፍኗል ወይ የሚለው መለካት ያለበት ከፓርቲው እድሜ አንፃር መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ምርጫው ይካሄዳል ወይ? በሚል ለቀረበው ጥያቄም ምላሽ ሲሰጡ የኢዜማ የመጀመሪያ አቋም የነበረው የተደላደለ ሁኔታ እስኪፈጠር ምርጫው ይራዘም የሚል ሀሳብ እንደነበር አውስተው መንግሥት ምርጫው መደረግ አለበት የሚል አቋም ሲያራምድ ምርጫ ቦርድም ምርጫው ይካሄዳል በሚል ዝግጅት ማድረጉን ሲቀጥል በምርጫው አማራጭ መኖር አለበት የሚል አቋም ኢዜማም ስለሚያራምድ ለምርጫው ዝግጅት መጀመሩን ገልፀዋል፡፡ ዋስትናችሁ ማን ነው? በሚል ለቀረበው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡም ዋስትናችን ሕዝብ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ጭቆናን የሚሸከም የኢትዮጵያ ወጣት የለም፡፡ የዴሞክራሲ ባለቤት ሕዝብ ነው፡፡ ስለዚህ ዋስትናችን የሚሆነውም ሕዝብ ነው ብለዋል፡፡ ከዚህ ቀደም ከነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች አደረጃጀቶች የተለየ አደረጃጀት ኢዜማ እንደሚከተልና ወረዳዎች ከማዕከል ሰው እንደማይሾምላቸውና ያለማንም ጣልቃገብነት ራሳቸውን ችለው ስለሚንቀሳቀሱ እንዲሁም ለምርጫ የራሳቸውን እጩዎች ስለሚያቀርቡ በወረዳው ነዋሪም ሆነ ሕዝብ እምነት የማይጣልበት ሰው የኢዜማ የወረዳ አመራር ስለማይሆን ወደ ማእከልም የሚመጣው በወረዳው የተመረጠ ሰው ስለሆነ ሌላ ዓላማ አንግቦ የሚንቀሳቀስ ግለሰብ ሰርጎ ገብ የሚሆንበት እድል እንደሌለ ጠቁመዋል፡፡

# የገቢ ማሰባሰቢያ የእራት መርሃ ግብር በስኬት ተጠናቀቀ

*ታኅሣሥ 9 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜናች መድረክ)*



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ታኅሣሥ 5 ቀን 2012 ዓ.ም በኢንተርኮንትኔንታል ሆቴል ያዘጋጀው የገቢ ማሰባሰቢያ የእራት መርሃ ግብር በስኬት መጠናቀቁን የገቢ እና ሀብት ማሰባሰብ ግብረ ኃይል አስተባባሪ የሆኑት አንድነት ሺፈራው ለዜጎች መድረክ ገለጹ፡፡

በእራት ፕሮግራሙ ለመታደም ፍቃደኛ የሆኑ ኢዜማን ያቅማቸው ያህል ለመደገፍ የፈለጉ በተለያየ የሀገራችን ክፍል የሚኖሩ ሰዎች ከ800 በላይ ትኬቶች መግዛታቸውን ከ600 በላይ የሆኑ ሰዎችም በዚህ ዝግጅት ላይ በአካል በመገኘት በእራት መርሃ ግብሩ ላይ ተሳትፈዋል፡ ፡ ትኬት ቆርጦ ከመግባትም ባለፈ የቃልኪዳን ሰነድ ላይ ኢዜማን በሙያ፣ በገንዘብ፣ በቁሳቁስ ለመርዳት ቃል የገቡ እንዳሉም አስተባባሪው ገልጸዋል፡፡

በዕለቱ የተገኘው የገቢ መጠን ለማወቅ ሙሉ ሥራ ተሰርቶ ስላልተጠናቀቀ ገቢ የሆነውን በእርግጠኝነት እስካሁን ማወቅ ያልተቻለ ቢሆን በቅርቡ ይፋ እንደሚደረግ ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም በዚህ ወር ውስጥ የተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ሥራዎች በስፋት እንደሚሠሩ በተለያዩ ክልሎችም በሚደረጉ ሕዝባዊ ስብሰባዎች ጭምር የገቢ ማሳባሰቢያ ሥራ እንደሚሰራ ታውቋል፡፡

በእራት ፕሮግራም ላይ የፓርቲው አባል ያልሆኑ ብዛት ያላቸው ኢትዮጵያዊያን የተገኙ ሲሆን አባል ለመሆን ፍላጎታቸውን አሳይተዋል፡፡ በቀጣይም የተለያየ ድጋፍ እንደሚያደርጉ በቃል ደረጃ ማረጋገጫ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ በፊት በሀገሪቱ ውስጥ የነበሩ ባለሀብቶች በፖለቲካ ውስጥ ምንም ዓይነት ሚና ውስጥ የማይሳተፉ የነበረ ሲሆን አሁን ግን በአዲስ መንፈስ በመነቃቃት ፖለቲካው ውስጥ ተሳትፎ ማድረግና መደገፍ መጀመራቸው የሚያበረታታ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በፕሮግራሙ ላይ ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም፣ ዶ/ር ኃይሉ አርአያ፣ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝን የመሳሰሉ በእራት ግብዣው ላይ በእንግድነት ተገኝተዋል፡፡